ትንቢተ ዮናስ (Jonah)

ምዕራፍ 1።

1፤ የእግዚአብሔርም ቃል ወደ አማቴ ልጅ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ።

2፤ ተነ ሥተህ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማወደ ነ ነ ዌ ሂድ፥ ክፉታቸውምወደ ፊቴ ውጥቶአልና በእርስዋ ላይ ስበክ።

3፤ ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ተርሴስ ይከብልል ዘንድ ተነ ሣ፤ ወደ ኢዮጴምወረደ፥ ወደ ተርሴስም የምታልፍ መርከብአገ ኘ፤ ከእግዚአብሔርምፊት ከመልሎከእነ ርሱ ጋር ወደ ተርሴስ ይሄድ ዘንድ ዋጋ ሰጥቶ ወደ እርስዋ ገ ባ።

4፤ እግዚአብሔርምበባሕሩ ላይ ታላቅ ነ ፋስን አመጣ፥ በባሕርምላይ ታላቅ ማዕበል ሆነ ፥ መርከቢቱም ልትሰበር ቀረበች።

5፤ መርከበኞቹምፈሩ፥ እያንዳንዳም ወደ አምላኩ ጮኸ፤ መርከቢቱምእንድትቀልልላቸውበወስጥዋ የነ በረውን ዕቃ ወደ ባሕር ጣሉት፤ ዮናስ ግን ወደ መርከቡ ወስጠኛውከፍል ወርዶ ነ በር፥ በከባድ እንቅልፍም ተኝቶ ነ በር።

6፤ የመርከበምአለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ። ምነ ውተኝተሃል? እንዳንጠፉ እግዚአብሔር ያስበን እንደ ሆነ ተነ ሥተህ አምላክህን ጥራ አለው።

7፤ እርስ በእርሳቸውም፡ ይህ ክፉ ነ ገር በማን ምክንያት እንዳገ ኘን እናወቅ ዘንድ ኑ፥ ዕጣእንጣጣል ተባባሉ። ዕጣምተጣጣሉ፥ ዕጣውምበዮናስ ላይ ወደቀ።

8፤ የዚያን ጊዜም፡ ይህ ክፉ ነ ገር በማን ምክንያት እንዳገ ኘን እባክህ ንገ ረን፤ ሥራህ ምንድር ነ ው? ከወዴትስ መጣህ? አገ ርህስ ወዴት ነ ው? ወይስ ከማን ወገ ን ነ ህ? አሉት።

9፤ እርሱም፡ እኔ ዕብራዊ ነ ኝ፤ በሰሩንና የብሱን የፈጠረውን የሰማይን አምላክ እግዚአብሔርን እመልካለሁ አላቸው።

10፤ እነ ዚያምሰዎች ከእግዚአብሔር ፊት እንደ ኰበለለ እርሱ ስለ ነ ገራቸውአወቁዋልና እጅግ ፈርተው። ይህ ያደረግኸውምንድር ነ ው? አሉት።

11፤ ባሕሩንምሞገ ዱአጥብቆ ያናውጠውነ በርና። ባሕሩ ከእኛ ዘንድ ጸጥ እንዲል ምን እናድርግብህ? አሉት።

12፤ እርሱም፡ ይህ ታላቅ ማዕበል በእኔ ምክንያት እንዳገ ኛችሁ አወቃለሁና አንሥታችሁ ወደ ባሕር ጣሉኝ፥ ባሕሩምጸጥ ይልላችኋል አላቸው።

13፤ ሰዎቹ ግን ወደ ምድሩ ሊመለሱ አጥብቀውቀዘፉ፤ ዳሩ ግን ባሕሩ እጅግ አብዝቶ ይናወጥባቸውነ በርና አልቻሉም፡

14፤ ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ጮኸው። አቤቱ፥ እንደ ወደድህ አድርገሃልና እንለምንሃለን፤ አቤቱ፥ ስለዚህ ሰውነ ፍስ እንዳንጠፉ ንጹሕምደምበእኛ ላይ እንዳታደርግ እንለምንሃለን አሉ።

15፤ ዮናስንምወስደውወደ ባሕሩ ጣሉት፤ ባሕሩምከማዕበጸጥ አለ።

16፤ ሰዎችምእግዚአብሔርን እጅግ ፈሩ፥ ለእግዚአብሔርምመሥዋዕትን አቀረቡ፥ ስእለትንምተሳሉ።

ምዕራፍ 2።

1፤ እግዚአብሔርምዮናስን የሚውጥ ታላቅ ዓሣ አሰናዳ፤ ዮናስምሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣውሆድ ወስጥ ነበረ።

2፤ ዮናስምበዓሣውሆድ ወስጥ ሆኖ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፥ እንዲህምአለ።

3፤ በመከራዬ ሳለሁ ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፥ እርሱምሰማኝ፤ በሲኦልምሆድ ወስጥ ሆኜ ጮኽሁ፥ ቃሌንምአዳመጥህ።

4፤ ወደ ጥልቁ ወደ ባሕሩ ወስጥ ጣልኸኝ፥ ፈሳሾችምበዙሪያዬ ነበሩ፤ ሞገድህና ማዕበልህ ሁሉ በላዬ አለፉ።

5፤ እኔምም፡ ከዓይንህ ፊት ተጣልሁ፤ ነገር ግን ወደ ቅዱስ መቅደስህ ደግሞእመለከታለሁ አልሁ።

6፤ ውኆችምእስከ ነፍሴ ድረስ ከበቡኝ፤ ጥልቁ ባሕር በዙሪያዬ ነበረ፤ የባሕሩ ሣር በራሴ ተጠመጠመነበር።

7፤ ወደ ተራሮች መሠረት ወረድሁ፤ በምድርና በመወርወሪያዎችዋ ለዘላለምተዘጋሁ፤ አንተ ግን፥ አቤቱ አምላኬ፥ ሕይወቴን ከጕድጓዱአወጣህ።

8፤ ነፍሴ በዛለችብኝ ጊዜ እግዚአብሔርን አሰብሁት፤ ጸሎቴምወደ አንተ ወደ ቅዱስ መቅደስህ ገባች።

9፤ ከንቱነ ትንና ሐሰትን የሚጠበቁ ምሕረታቸውን ትተዋል።

10፤ እኔ ግን በምስጋና ቃል እሠዋልሃለሁ፤ የተሳልሁትንምእከፍላለሁ። ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

11፤ እግዚአብሔርምዓሣውን አዘዘው፥ እርሱምዮናስን በየብስ ላይ ተፋው።

ምዕራፍ 3።

1፤ የእግዚአብሔርምቃል ሁለተኛ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ፡

2፤ ተነ ሥተህ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማወደ ነነዌ ሂድ፥ የምነግርህንምስብከት ስበክላት አለው።

3፤ ዮናስምተነ ሥቶ እንደ እግዚአብሔር ቃል ወደ ነነዌ ሄደ፤ ነነዌምየሦስት ቀን መንገድ ያህል እጅግ ታላቅ ከተማነ በረች።

4፤ ዮናስምየአንድ ቀን መንገድ ያህል ወደ ከተማይቱ ወስጥ ሊገባ ጀመረ፤ ጮኾም፡ በሦስት ቀን ወስጥ ነነዌ ትገ ለበጣለች አለ።

5፤ የነነዌምሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ፤ ለጾምአዋጅ ነገሩ፥ ከታላቁምጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ ማቅ ለበሱ።

6፤ ወሬውምወደ ነነዌ ንጉሥደረሰ፤ እርሱምከዙፋኑ ተነሥቶ መጐናጸፊያውን አወለቀ ማቅምለበሰ፥ በአመድም ላይ ተቀመጠ።

7፤ አዋጅምአስነገረ፥ በነነዌምወሰጥ የንጉሣንና የመኳንንቱን ትእዛዝ አሳወጀ፥ እንዲህምአለ። ሰዎችና እንስሶች ላሞችና በጎች አንዳችን አይቅመሱ፤ አይሰሙምውኃንምአይጠጡ፤

8፤ ሰዎችና እንስሶችምበማቅ ይከደኑ፥ ወደ እግዚአብሔርምበብርቱ ይጩኹ፤ ሰዎችምሁሉ ከክፉ መንገዳቸውና በእጃቸውካለውግፍ ይመለሱ።

9፤ እኛ እንዳንጠፋ እግዚአብሔር ተመልሶ ይጸጸት እንደ ሆነ ፥ ከጽኑ ቍጣውምይመለስ እንደ ሆነ ማን ያውቃል?

10፤ እግዚአብሔርምከክፉ መንገዳቸውእንደተመለሱ ሥራቸውን አየ ፤ እግዚአብሔርምያደርግባቸውዘንድ በተናገረውክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም።

ምዕራፍ 4።

1፤ ይህምዮናስን ከቶ ደስ አላሰኘውም፥ እርሱምተቈጣ።

2፤ ወደ እግዚአብሔርምጸለየና። አቤቱ፥ እለምንሃለሁ፤ በአገሬ ሳለሁየተናገርሁት ይህ አልነበረምን? አንተ ቸርና ይቅር ባይ፥ ታጋሽም፥ ምሕረትህምየበዛ፥ ከክፉውነገርምየተነሣየምትጸጸት አምላክ እንደ ሆንህ አውቄ ነበርና ስለዚህ ወደ ተርሴስ ለመኰበለል ፈጥኜ ነበር።

3፤ አሁንም፥ አቤቱ፥ ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ፥ ነፍሴን ከእኔ ወሰድ አለው።

4፤ እግዚአብሔርም፡ በውኑ ትቈጣዘንድ ይገባሃልን? አለ።

5፤ ዮናስምከከተማይቱ ወጣ ከከተማይቱምበስተ ምሥራቅ በኩል ተቀመጠ፤ ከተማይቱንምየሚገኛትን እስኪያይ ድረስ በዚያ ለራሱ ዳስ ሠርቶ ከጥላውበታች ተቀመጠ።

6፤ እግዚአብሔር አምላክምቅል አዘጋጀ፥ ከጭንቀቱምታድነ ውዘንድ በራሱ ላይ ጥላ እንድትሆን በዮናስ ላይ ከፍ ከፍ አደረጋት፤ ዮናስምስለ ቅሊቱ እጅግ ደስ አለው።

7፤ በነጋውግን ወገግ ባለ ጊዜ እግዚአብሔር ትልን አዘጋጀ፥ እርስዋምቅሊቱን እስክትደርቅ ድረስ መታቻት።

8፤ ፀሐይምበወጣች ጊዜ እግዚአብሔር ትኩስ የምሥራቅ ነፋስ አዘጋጀ ዮናስ እስኪዝል ድረስምፀሐይ ራሱን መታው፤ ለራሱምሞትን ፈለገ። ከሕይወት ሞት ይሻለኛል አለ።

9፤ እግዚአብሔርምዮናስን። በውኑ ስለዚች ቅል ትቈጣዘንድ ይገባሃልን? አለው። እርሱም፡ እስከ ሞት ድረስ እቈጣዘንድ ይገባኛል አለ።

10፤ እግዚአብሔርም፡ አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምህባት ላላሳደግሃትም፡ በአንድ ሌሊት ለበቀለች፥ በአንድ ሌሊትምለደረቀችውቅል አዘነሃል።

11፤ እኔስ ቀኛቸውን ና ግራቸውን የ ሚ ለዩ ከ መ ዞ ሀያ ሺህ የ ሚ በ ልጡ ሰ ዎች ና ብዙ እ ን ስ ሶ ች ላ ሉ ባ ት ለ ታ ላ ቂ ቱ ከ ተ ማ ለ ነ ነ ዌ አ ላ ዝ ን ም ን? አ ለ ው።